# አዲስ፡ዓመት

ከራስህ፡ጋር፡ሳትታረቅ፤

ጠላት፡ሆነህ፡ስትዘባርቅ፤

አንተነትህን፡ሳይናገር፡ሳያሳውቅ፤

የእጅህን፡ሰጥቶ፡ሳይሳለቅ፤

አዲሱ፡ዓመት፡አሮጌነቱን፡መቼም፡አይለቅ።

መች፡ሆነና፡ማቅ፡መልበሱ፤

ትቢያና፡አመድ፡መነስነሱ፤

በድንጋይ፡ላይ፡መንተራሱ፤

ለአዲሱ፡ዓመት፡መገስገሱ።

ልብስ፡መቅደድ፡ፅድቅ፡ሆነና፤

የልብ፡ጉዳይ፡ተረሳና፤

የኔ፡ቢጤው፡ትዕቢተኛ፤

አሮጌውን፡ይዞት፡ተኛ፤

ላይመለስ፡ላይፀፀት፡ሁሌ፡ለመሆን፡ገበነኛ።

ታዲያ፡ይሄ፡ነው፡የፅድቅ፡ሥራ፤

የሚያስታረቅ፡ከአምላክ፡ጋራ፤

ዮሐንስ፡የሰበከው፤

በምድረ፡በዳ፡ንስሐ፡ግቡ፡እያለ፡ያስተማረው፤

ነበር፡እንጂ፡ለመለየት፡ከእፉኝነት፤
ልብስን፡ሳይሆን፡ልብን፡ቀዶ፡ለመገኘት፤
አሮጌውን፡ገፎ፡ጥሎ፤
ለመዋደድ፡ከአዲሱ፡ዓመት።
ታዲያ፡እንበርታ፡ለመታየት፤
እንደ፡አደይ፡አበባ፡ፈክቶ፤
እንደ፡መልካም፡ፍሬ፡ፈርቶ፤
እንደሚያውድ፡ሽቶ፡ሸቶ፤
አሮጌው፡በአዲስ፡ተተክቶ፤
ለሰማያዊ፡ክብር፡ታጭቶ፤
መገኘቱ፡አያኮራም?
እሰየውስ፡አያሰኝም፤
ክርስቲያንስ፡አያስብልም፤
ይታወቃ! መታደሱ፤
በበረከት፡መቀደሱ፤
በአምላክ፡ቃል፡መፈወሱ።
ይገለፃ!መፅሐፉ፤
እንዲነበብ፡በየምዕራፉ፤
አጋንንቶች፡እንዲጠፉ።

እረ!ይከበር፡ዓመት፡በዓሉ፤
ሰዎች፡ሁሉ፡ዕልል፡በሉ፤
ተሰብሰቡ፡ይሰማ፡ቃሉ።
አፍሩ፡ፍሬ፡መክሊት፡ይብዛ፤
እንዳንጠፋ፡እንደጤዛ፤
ጨዋታችን፡አይጎምዝዛ።
ይሁን፡አንደበት፡የማር፡ወለላ፤
ለሁሉም፡ይሰጥ፡ደስታ፡ተድላ፤
መቅረዛችን፡እየሞላ።
ብርሃናችን፡በሰው፡ፊት፡ይብራ፤
ሐሰት፡ትሙት፡ትውረድ፡ከስራ፤
ዕውነት፡ትቁም፡ከኛ፡ጋራ፤
የአዲሷ፡ዓመት፡ይህ፡ነው፡ክብሯ።
የዓመት፡በዓል፡ጣዕሙ፤
ማጣፈጫው፡ቅመሙ፤
የዕለት፡የቀን፡ትርጉሙ፤
መተሳሰብ፡ነው፡ማህተሙ።
የሚነደው፡እሳቱ፤
የሚብሰው፡ክፋቱ፤

የሚቀርበው፡ሽንፈቱ፤

ሰው፡ሰውን፡ሲያነሳው፡ነው፡በከንቱ፤

ሲቀጣጠል፡ሃሜቱ፤

የዓመት፡በዓል፡መረሳቱ።

የትአል፡ታዲያ! መመለሱ፤

የዓመት፡በዓል፡ዋዜማ፡ጥንስሱ፤

የአንተ፡ትብስ፡አንቺ፡ትብሽ፡መንፈሱ፤

የተበደለን፡መካሱ፤

የዲያብሎስን፡ስራ፡ማርከሱ(ማፍረሱ)፤

ይፈታ፡በዓመት፡በዓሉ፤

ወሬ፡ይዞ፡ማንጠልጠሉ፤

ገበታ፡ላይ፡መጣጣሉ፤

አንዱ፡ሌላውን፡ማቃለሉ።

ሆድ፡ሲያውቅ፡ዶሮ፡ማታ፤

የምትመስለዋ፡ሰላምታ፤

ያቺ፡የጥርስ፡ብልጭታ፤

ባለ፡ደረቋ፡ፈገግታ፤

የማታመጣ፡መስሎን፡ስሞታ፤

ስናባብላት፡ለታይታ፤

ዋ! ይድረስና፡ዓመት፡በዓሉ፤
እንዳይታዘበን፡ሰው፡ሁሉ፤
እንንቃ፡አንተኛ፡ለቃሉ፤
ለእውነተኛው፡መንገድ፡ወንጌሉ፤
እንዲቀበለን፡በዓሉ።
ድምፅ፡አምሮ፡ቢያስተጋባ፤
ቅላፄው፡ሆድ፡ቢያባባ፤
ምግባር፡ሳይኖር፡የት፡ሊገባ፤
አዲስ፡ዓመት፡አይሆን፡አምባ፤
ውጪ፡ያስጥላል፡እንደሌባ።
አዋቂው፡እንደህፃን፡ሲጣላ፤
ከአውሬ፡አንሶ፡ሲበላላ፤
መንገድ፡ሲሻ፡ለብቀላ፤
ለራስ፡ብቻ፡እያደላ፤
ይባል፡ይሆን፡ጥሩ፡ኑሮ፤
ያደርስስ፡ይሆን፡አስከብሮ፤
ለአዲሱ፡ዓመት፡በቀጠሮ፤
እኔ፡እንጃልኝ፡ልቤ፡ፈራ፤
አላየውም፡ያን፡አዝመራ፤

ካልወጣሁኝ፡ከመከራ፤
ሆኖብኛል፡ያ፡ስጋዬ፡ባላጋራ።
የዐይኔ፡የዕንባ፡ቋጠሮ፤
ላይቀር፡ከውስጥ፡ተቀብሮ፤
ላያስመስል፡ለልብ፡ነግሮ፤
ወረድኩ፡ይላል፡ተንቆርቁሮ፤
ቢብስበት፡እንጉርጉሮ፤
እንዲህ፡እያለ፡አመሥጥሮ፤
አይ! ዓመት፡በዓል፡ያ! የጥንቱ፤
ፍልቅልቁ፡ደግ፡ፊቱ፤
ለግላጋው፡ልጅነቱ፤
ገራገሩ፡ያ፡ ትሁቱ፤
ያሳዝናል፡ሰንበቱ፤
አልገኝ፡ሲል፡ውልቃቱ፤
ልቅሶ፡ሲሆን፡ምሳ፡እራቱ፤
ላይመለስ፡ካልተመለስን፤
ዳግም፡ላያየን፡ካልተዋደድን፤
ጆሮ፡ዳባ፡ይላል፡ዘመን።

ከኃይለመስቀል፡ተስፋዬ (ከለንደን)